# የኃይል መቋረጥ ሲከሰት ምን ማድረግ ያስፈልጋል

Public Health
Seattle & King County

## ሁሉም የምግብ ተቋማት

### 1 ክንዋኔዎችን ማቆም አለባቸው




- ይህም ማለት፡- የምግብ ዝግጅትም ሆነ አገልግሎት አይኖርም
- የሃይል መቋረጡ የተከሰተበትን ሰአት ይመዝግቡ




PHF የሚከተሉትን ያካትታል፡- ከፍተኛ የፕሮቲን ምግቦች (ሥጋ፣ ዶሮ፣ ዓሣ፣ እንቁላል፣ የወተት ተዋጽኦ፣ አይብ)፤ የበሰለ ሩዝ፣ ባቄላ፣ ድንች፣ ፓስታ፣ አትክልት፤ ድንች / ፓስታ ሰላጣ፤ custards / puddings



### 2 ኃይል በጠፋ ሰዓት

- የ PHFን ሙቀት መጠን ይመልከቱ
  - ሃይል በተቋቀረጠ ሰዓት 41 F ወይም ከዚያ በታች የሆነ PHF፡ ያቀዝቅዙ
  - ሃይል በተቋቀረጠ ሰዓት ከ41 F - 135 F ውስጥ ያለ PHF፡ አውጥተው ይጣሉ
- የበረዶ ከረጢቶችን በማቀዝቀዣ/ፍሪዘር ውስጥ ያስቀምጧቸው
- የፍሪጅ እና የፍሪዘር በሮችን ዝግ እንደሆኑ ያቆዩዋቸው




### 3 ሃይል ወደ ነበረበት ከተመለሰ በኋላ

- ሃይል ሲመለስ ቀዝቃዛ መያዣዎችን ይመልከቱና ከ 41°F በላይ የሆኑ PHF አውጥተው ይጣሉ ወይም የትኛው ምግብ ለማስቀመጥ ወይም ለማቅረብ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ለሚለው መመሪያ ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይጠቀሙ። ጊዜው የማይታወቅ ከሆነ ይጣሉት።
- የሚከተሉትን ክንዋኔያቸውን ይመልከቱ፡-
  - ✔ ማቀዝቀዣዎች / ፍሪዘሮች
  - ✔ ሙቅ እና ቀዝቃዛ የሚጠጣ ውሃ
  - ✔ ትኩስ ምግብ መያዣ ስርአቶች
  - ✔ የማናፈሻ ስርአቶችን
  - ✔ የማብሰያ እቃዎች
- በረዶ እንደሆነ ጠንክሮ የቀረ ምግብ ሊቀመጥ ይችላል

## የቀዝቃዛ ምግብ ሙቀት መጠን እና የመያዣ ሰዓት መመሪያዎች

| ጊዜ | ከ 42° እስከ 45° F | ከ 46° እስከ 55° F | 56° F ወይም ከዛ በላይ |
|---|---|---|---|
| ከ 0 እስከ 4 ሰአታት | ለመሸጥ አስተማማኝ የሆነ | ወዲያውኑ 41° F ድርስ ያቀዝቅዙት | 165° F ድረስ በድጋሚ ያሙቁት |
| ከ 4 እስከ 12 ሰአታት | ለመሸጥ አስተማማኝ የሆነ | ወዲያውኑ 41° F ድርስ ያቀዝቅዙት | PHF ሊሸጥ አይችልም፣ ምግቡን ይጣሉት |
| ከ 12 ሰአታት በላይ | ወዲያውኑ 41° F ድርስ ያቀዝቅዙት | PHF ሊሸጥ አይችልም፣ ምግቡን ይጣሉት | PHF ሊሸጥ አይችልም፣ ምግቡን ይጣሉት |

ለማናቸውም ጥያቄዎች እና ዳግም ለመከፈት ፈቃድ ለማግኘት የሕዝብ ጤና ክፍልን ያነጋግሩ 206-263-9566

ዝርዝር መመሪያዎችን ለማግኘት ሌላኛውን ጎን ይመልከቱ።

# የኃይል መቋረጥ ሂደቶች ዝርዝር መመሪያዎች

ሁሉም የምግብ ተቋማት የኃይል መቋረጥ ሲከሰት የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው ፍቃድ ለማግኘት ወወይም ለጥያቄ የጤና ከፍል ብ በዚህ ቁጥር ይደውሉ፡ 206-263-9566

አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ምግቦች (PHF): ከፍተኛ የፕሮቲን ምግቦች (ሥጋ፣ ዶሮ፣ ዓሣ፣ እንቁላል፣ የወተት ተዋጽኦ፣ አይብ); የበሰለ ሩዝ፣ ባቄላ፣ ድንች፣ ፓስታ፣ እና አትክልት፤ ድንች / ፓስታ ሰላጣ፤ custards / puddings፤ አረንጓዴ ቅጠላማዎችን ይቁረጡ እና ሌሎች ተመሳሳይ ምግቦችን ያካትታል።

## 1 ክንዋኔዎችን ማቆም አለባቸው

የኃይል መቋረጥ በሚከሰት ጊዜ ተቋማት መዘጋት አለባቸው።
የኃይል መቋረጡ የተከሰተበትን ጊዜ ይመዝግቡ።




## 2 ኃይል በጠፋ ሰዓት

- የ PHFን ሙቀት መጠን ይመልከቱ
  - ሃይል በተቋቀረጠ ሰዓት 41 F ወይም ከዚያ በታች የሆነ PHF፡ ያቀዝቅዙ
  - ሃይል በተቋቀረጠ ሰዓት ከ41 F - 135 F  ውስጥ ያለ PHF፡ አውጥተው ይጣሉ
- የበረዶ ከረጢቶችን በማቀዝቀዣዎች/በረዶ ቤቶች ውስጥ ያስቀምጡ፡፡ ደረቅ በረዶ በጠባብ ቦታ መጠቀም የለባችሁም፡፡ የማቀዝቀዣ እና የበረዶ ቤቶች በሮችን በሁሉም ጊዜ መዝጋት አለብዎ
- ሙቅ ምግብን በፍሪጆች ወይም በፍሪዘሮች ውስጥ አያስቀምጡ። ከ 4 ሰአታት በህዋላ ከ 135 F  በታች የሆኑ ሁሉንም PHF ያስወግዱ። በ 4 ሰአታት ውስጥ ሙብራት ተመልሶ የሚመጣ ከሆነ፣ ምግቡን እስከ 165F ድረስ ዳግም ያሙቁ።







## 3 ሃይል ወደ ነበረበት ከተመለሰ በኋላ

ተቋሙን መልሰው ከመክፈትዎ በፊት እነኚህን መመሪያዎች ይከተሉ። የህዝብ ጤና ክፍልን ለፍቃድ ወይም ለጥያቄዎች ያናግሩ፡- 206-263-9566።

የ PHF አያያዝ እና አወጋገድ – ከ 41°F በላይ የሆነን PHF ለመለየት ንጹህና በማጽጃ ፈሳሾች የጠራ ዲጂታል የሙቀት መለኪያ ይጠቀሙ። ተቃራኒ ገጽ ላይ ያለው ሰንጠረዥ  ላይ PHF እንዴት መያዝ እና ማስወገድ እንደሚቻል መመሪያዎችን ይመልከቱ። ሰአቱ የማይታወቅ ከሆነ፣ ያስወግዱት  እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ይጣሉት!

በረዶ የሆነ ምግብ – ምግቡ ጠጣር እንደሆነ ከቆየ እና የመቅለጥ ምልክት፣ እንደ ማላብ፣ አካላዊ ቅነሳ ወይም የመያዣ ጉዳት ከሌለ ምግቡ ሊቀመጥ ይችላል። ያለበለዚያ፣ ይጣሉት።

የሚከተሉትን ስርአቶች ይመልከቱ፡-



የማናፈሻ ስርአቶች፡- በመሽከርከር የሚሰራው የማናፈሻ ስርአት የማብሰል ስራው ከመጀመሩ በፊት መስራት አለበት



የሞቀ አያያዝ – የሞቀ መያዣ እቃ 135°F ወይም ከዚያ በላይ መያዙን



ማቀዝቀዣ –  ማቀዝቀዣዎች 41°F ወይም ከዚያ በታች መሆናቸውን



ውሃ – ከቧንቧ የሚወርደው የሞቀ ውሃ ቢያንስ 100°F መሆኑን

---



## ደህና ይሁኑ!

አይጠቀሙ፡- የከሰል፣ የእንጨት ወይም የጋዝ ማብሰያ እቃዎችን ወይም ተንቀሳቃሽ ጄነሬተሮችን በቤት ውስጥ!



170531_8319w_DPH_fact_power_outage.ai